የሰ/መ/ቁጥር 237523

ጥቅምት 07 ቀን 2016 ዓ/ም

ዳኞች ፡- ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

እንዳሻው አዳነ

ተሾመ ሽፈራው

መላኩ ካሳዬ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡- ቢኬደብሊው አርክቴክት፣ ፕላነር፣ አማካሪ እና ኢንጂነሪንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር - ጠ መክብብ ስጥይበል - ቀረቡ

ተጠሪ፡- የገቢዎች ሚኒስቴር ነ/ፈ በለጠ ሙሉ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

ጉዳዩ አመልካች በተጠሪ ተጨማሪ የትርፍ ግብር እና የተጨማሪ እሴት ታክስ እንዲከፍል የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም የቀረበ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ለዚህ ሰበር ቅሬታ መነሻ የሆነው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 288141 በነሐሴ 26 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ነው፡፡

ክርክሩ በተጀመረበት በፌደራል ታክስ ይግባኝ ኮሚሽን የአሁን አመልካች የተጠሪን ውሳኔ በመቃወም የይግባኝ ቅሬታ አቅርቦ ኮሚሽኑ ተጠሪን አስቀርቦ ካከራከረ በኋላ የተጠሪን ውሳኔ በማጽናቱ አመልካች የይግባኝ ቅሬታ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የአመልካችን ቅሬታ አስቀርቦ

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ካከራከረ በኋላ የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን የሰጠውን ውሳኔ አጽንቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ላይ በህዳር 20 ቀን 2015 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር ቅሬታ አቅርቦ የሰበር አጣሪ ችሎት የአመልካች ቅሬታ እንዲጣራ ተጠሪ መልስ እንዲያቀርብ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ በጥር 15 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው መልስ አመልካች ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ የማቅረብ እድሉን ሳይጠቀም በቀጥታ የሰበር ቅሬታ ያቀረበ በመሆኑ የሰበር ቅሬታው ውድቅ ይደረግልኝ የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርቧል፡፡ አመልካች በበኩሉ በየካቲት 07 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የመልስ መልስ በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 58 መሰረት ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሊቀርብ የሚችለው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን የሰጠውን ውሳኔ ቢያሻሽል ወይም ቢሽር ኖሮ ነበር፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የኮሚሽኑን ውሳኔ ያጸና በመሆኑ በቀጥታ የሰበር ቅሬታ ማቅረቤ ተገቢ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

እኛም የአመልካች ቅሬታ ያስቀርባል ሲባል የተያዘውን ጭብጥ ከመመርመራችን በፊት አመልካች የሰበር ቅሬታ ያቀረበው የመጨረሻ ውሳኔ ባገኘ ጉዳይ ላይ መሆን ያለመሆኑን ከተገቢው የህግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው በዚህ ሰበር ችሎት ቅሬታ የቀረበበት ጉዳይ የተጀመረው በፌደራል ታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ነው፡፡ በኮሚሽኑ ውሳኔ ላይ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ ቅሬታ ቀርቦ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ ላይ በቀጥታ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ቅሬታ የቀረበ መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ እንደሚታወቀው በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3/ሀ) እና በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10 መሰረት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉን የመጨረሻ ዉሳኔዎች በማረም ላይ የተገደበ ነዉ፡፡ የመጨረሻ ውሳኔ ማለት ምንማለት ነው? የሚለውን በተመለከተ በፌደራል ፍርድ ቤቶች እና በክልል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ እንዲሁም በሌሎች ህጎች በተመለከተው መሰረት ጉዳዩ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ከመቅረቡ በፊት በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ለመስጠት ስልጣን ያለው አካል የሰጠው ውሳኔ ማለት መሆኑን ከአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10 መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም በህግ ለዚህ ሰበር ችሎት ቅሬታ ከመቅረቡ በፊት የመጨረሻ ውሳኔ የመስጠት ስልጣን የተሰጠው አካል የመጨረሻ ውሳኔ ሳይሰጥ በቀጥታ የሰበር ቅሬታ ቢቀርብ ቅሬታው በዚህ ችሎት ለመታየት ብቁ ሊሆን አይችልም፡፡

የተያዘው ጉዳይ ከታክስ ጋር የተያያዘ በመሆኑ ተፈጻሚነት የሚኖረው የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 ነው፡፡ በዚህ አዋጅ ከታክስ ጋር በተገናኘ የሚፈጠሩ አለመግባባቶች የሚፈቱበት ሂደት በአንቀጽ 52 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ላይ ተመልክቷል፡፡ በተለይም በአዋጁ ከአንቀጽ 55-58 ከታክስ ውሳኔ ጋር የተያያዙ ቅሬታዎች መጀመሪያ በተጠሪ ለሚቋቋም አጣሪ ኮሚቴ መቅረብ እንዳለበት፣ የአጣሪ ኮሚቴው በሚሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን ይግባኙን ለታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ማቅረብ እንደሚችል፣ በኮሚሽኑ ውሳኔ ላይ የህግ ስህተት ተፈጽሟል የሚል ወገን ደግሞ የይግባኝ ቅሬታ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከዛም ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማቅረብ የሚችል መሆኑ ተደንግጓል፡፡ በእነዚህ ድንጋጌዎች መሰረት

*ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

ከታክስ ውሳኔ ጋር ተያይዞ የሚፈጠሩ ቅሬታዎች መቅረብ የሚገባቸው ለየትኛው አካል እንደሆነ በልዩ ሁኔታ የተደነገገ በመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 58 መሰረት በታክስ ጉዳይ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ የመስጠት ስልጣን ያለው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት መሆኑን ያመለክታል፡፡ አመልካች የከፍተኛ ፍርድ ቤት የኮሚሽኑን ውሳኔ ያልቀየረው ወይም ያጸናው በመሆኑ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ ሊቀርብ አይችልም በሚል የሚከራከር ቢሆንም በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10/1/ሀ በመደበኛ ፍርድ ቤት ተጀምረው በይግባኝ በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ታይተው የጸኑ ጉዳዮችን የሚመለከት እንጂ በልዩ ሕግ የመጨረሻ ውሳኔ የመስጠት ስልጣን የተሰጣቸውን አካላት የመጨረሻ ውሳኔ ከመስጠት የሚያግዳቸው አይደለም፡፡

በአጠቃላይ አመልካች ለዚህ ሰበር ችሎት ቅሬታ ያቀረቡት የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን እና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሳኔ በአዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 58/3 መሰረት በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ታይቶ የመጨረሻ ውሳኔ ሳያገኝ በመሆኑ ለሰበር ብቁ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም የአመልካች ቅሬታ ተሰርዟል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም